የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44 208 1335670 pr@ginbot7.org

ቀን፡ ሚያዝያ 17/ 2001 ዓ.ም

# ከግንቦት 7 ለፍትህ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ጉዳዩ፡ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን፣ በዛሬው እለት፣ ሚያዝያ 17/2001 ግንቦት 7 ንቅናቄን በሚመለከት በወያኔ የዜና አውታሮች አገዛዙ ያሰራጨውን መግለጫ በሚመለከት ለቀረቡልን ጥያቄዎች የተሰጠ ማብራሪያ።

የመለስ አገዛዝ በዛሬው እለት ሚያዝያ 17/ 2001 ዓ.ም ‹ራሱን የግንቦት 7 ብሎ የሚጠራው ቡድን የሽብር ሴራ ከሸፈ› በማለት ያወጣውን መግለጫ አንብበነዋል። የመለስ አገዛዝ በተለያዩ ወቅቶች በህዝብ ውስጥ ተቃውሞ ሲበዛበት፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች አፋጠው ሲይዙት፣ በገዛ ሰራዊቱና በሲቪል አስተዳደሩ ውስጥ ችግር በገጠመው ቁጥር፣ ህዝብን ለማደናገር ወይም የሚፈልጋቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች ለማጥቃት ሰፈልግ እንዲህ አይነቱን መግለጫ ማውጣትና ህዝብን ማደናገር፣ መግለጫውን ተከትሎ የሚፈልገውን መግደል፣ ማሰር፣ ከስራ ማባረር፣ ከቀየው ማፈናቀልና ማሳደድ ባለፉት አስራ ስምንት አመታት እድሜው ደጋግሞ ሲፈጽመው የኖረ ነውረኛ ድርጊቱ እንደሆነ ይታወቃል።

ይህ በዛሬው እለት ግንቦት 7 ንቅናቄን በሚመለከት ያወጣው መግለጫ ከእዚህ በፊቱ ወያኔ ሲያወጣው ከነበሩት መግለጫዎች ልዩነት የሌለው መሆኑን ንቅናቄያችን ይገልፃል። የሚይዘው የሚጨብጠው ያጣው የመለስ አገዛዝ የግንቦት 7ን ንቅናቄ በማንሳት አንዴ በሰላም እንቀሳቀሳለን የሚሉ ድርጅት አባላት በስውር የግንቦት 7 አባላት ናቸው የሚል የስም ዝርዝር ሲያወጣ፣ አንዴም እነዚህ ከበርቴዎች ግንቦት 7ን ይደግፉሉ በማለት የማሸበሪያ ወረቀት ውስጥ ውስጡን ሲበትንና ባለሃብቶቹን ሲዘርፍ፣ አሁን ደግሞ የተወሰኑ የሰራዊት አበላት የግንቦት 7 ሰዎች ሆነው ተገኙ ብሎ በሬድዮና በቴለቪዝን ሲያስተጋባ ግንቦት 7 ንቅናቄ እየተነሳ ምላሽ በመስጠት የሚያጠፋው ጊዜ እንደሌለው ለማሳወቅ እንወዳለን።

ንቅናቄያችን እንደተገነዘበው ግንቦት 7 ለመለስ ዜናዊና በአምባገነናዊ ክበቡ ለተሰባሰቡት ጥቂት ዘረኞች እንቅልፍ የነሳቸው ድርጅት መሆኑን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ተገቢ ነው። ንቅናቄያችን የወያኔን ማስፈራሪያ ክስና ሌላም ነገር ፈርቶ ይህን ዘረኛ አምባገነን ስርአት ከሃገራችን ህዝብ ጫንቃ ላይ በማንሳት ህዝብ የሃገሩና የህይወቱ ባለቤት የሚሆንበትን መራራ ትግል በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር የጀመረውን ፍልሚያ አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ወዳጅም ሆነ በመለስ ዜናዊ ስር የተሰባሰቡት አማባገነን ዘረኞችና ደጋፊዎቻቸው ሊያውቁት ይገባል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
ሚያዚያ 17/2001 ዓ.ም